የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
Information Network Security Administration

# በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች ደህንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር አዋጅ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር --/2016

ረቂቅ ጽሑፍ

**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

**ሚያዝያ 2016 ዓ.ም**

# የመመሪያው ይዘት


1) አጭር ርዕስ ..... 1
2) ትርጓሜ ..... 1
3) ክልከላ የተጣለባቸው ምርቶች ..... 2
4) ክልከላ ለተጣለባቸው ምርቶች ስለሚሰጥ ልዩ ፈቃድ ..... 2
5) ገደብ ስለተጣለባቸው ምርቶች ..... 3
6) ክልከላና ገደብ የተጣለባቸው ምርቶችን ዝርዝር ስለማሻሻል፤ ..... 3
7) አዲስ ወይም ክሱት ምርቶችን ስለመሰየም ..... 4
8) ክልከላና ገደብን ስለማሳወቅ ..... 4
9) ስለ ደህንነት ማረጋገጫ ፍቃድ ..... 5
10) ወደ ሀገር ለማስገባት ስለሚሰጥ ፈቃድ ..... 5
11) ስለቅድመ-ፈቃድ ..... 6
12) ወደ ውጭ ለመላክ ስለሚሰጥ ፈቃድ ..... 6
13) ለማምረት፣ ለመገጣጠም ወይም ለመፍጠር ስለሚሰጥ ፈቃድ፤ ..... 7
14) ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት ለማከናወን ስለሚሰጥ ፈቃድ ..... 8
15) ማመልከቻ ስለማቅረብ ..... 8
16) ማመልከቻ ስለማቅረቢያ ጊዜ ..... 9
17) ምላሽ ስለመስጠት ..... 9
18) ስምምነት ስለመግባት ..... 10
19) ፈቃድ ስለማደስ ..... 10
20) ፈቃድ የሚሰረዝባቸው ሁኔታዎች ..... 10
21) ክትትል እና መረጃ አያያዝ ..... 11
22) ተቆጣጣሪ ስለሚሰየምባቸው መስፈርቶች፣ ..... 11
23) የተቆጣጣሪዎች ሙያዊ የስነምግባር ግዴታዎች ..... 12
24) ስለተቆጣጣሪ ስለመደብና ቁጥጥር ስለማድረግ፤ ..... 13
25) ስለተቆጣጣሪዎች ስራ ከባቢና ፕሮቶኮል ..... 13
26) ምርቶች ስለማስቀመጥ፤ ..... 14
27) ምርቶች ጥቅም ላይ ስለማዋል ..... 14
28) ምርቶች ስለሚወገዱበት አግባብ ..... 15
29) ቅሬታ ስለማቅረብ ..... 15
30) ቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜና ቦታ ..... 16
31) ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ስለማቋቋ ም ..... 16
32) የኮሚቴው አባላት ..... 16
33) የኮሚቴው ስብሰባ ..... 16
34) አባልነት ስለመሰረዝና ከስብሰባ ስለመነሳት ..... 17
35) ቅሬታን ስለማጣራት ..... 17
36) ውሳኔ ስለመስጠት ..... 17
37) መረጃ ስለመጠየቅና መቀበል ..... 18
38) ተጠያቂነት ..... 18
39) ስለመመሪያው መሻሻል ..... 18
40) የስራ ማንዋል እና ኮታሎግ ስለማውጣት ..... 18
41) ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች ..... 18
42) ስለተፈጻሚነት ጊዜ ..... 18

# መመሪያ ቁጥር ---/2016

# የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂምርቶች ደህንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር አዋጅ ማስፈፀሚያ መመሪያ

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች የደህንነት ማጋገጫ እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1310/2016 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1፣ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3፣ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 3፣ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 (ሠ)፣ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 2፣ አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 7፣ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 1 (በ) እና 2፣ አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 6፣ አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 2፣ አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 2፣ አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 1፣ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1) አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች የደህንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር .... /2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2) ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"አዋጅ"** ማለት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች የደህንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1310/2016 ነው፤
2. በአዋጁ አንቀፅ 2 ሥር ለተመለከቱት ቃላት የተሰጠው ትርጓሜ ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናል፤
3. **"ምርት"** ማለት የኤሌክትሮኒክ ዳታዎችንና ሲግናሎችን ለማነፍነፍ፣ ለማስተጓጎል፣ ለመጥለፍ፣ ለመደምሰስ፣ ለማሳሳት፣ ለማወክ፣ ለመስረቅ እና ተዓማኝነት ለማሳጣት የሚያስችል እና በኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ስጋት ሊፈጥር የሚችል የቴክኖሎጂ ቁስ፣ ንድፍ፣ ስልተ-ቀመር፣ ዘዴ፣ አገልግሎት ወይም መተግበሪያን ያጠቃልላል፤
4. **"ክልከላ የተደረገበት ምርት"** ማለት በሀገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ሊያደርስ ከሚችለው ስጋት አንፃር በዚህ አዋጅ መሠረት ወደ ሀገር እንዳይገባ፣ ከሀገር እንዳይወጣ ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውል ሙሉ ክልከላ የተጣለበት የቴክኖሎጂ ምርት ነው፤
5. **"ገደብ የተደረገበት ምርት"** ማለት በኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ሊያደርስ ከሚችለው ስጋት አንፃር በዚህ አዋጅ መሠረት አግባብነት ባለው የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ብቻ ወደ ሀገር እንዲገባ፣ ከሀገር እንዲወጣ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል ገደብ የተደረገበት የቴክኖሎጂ ምርት ነው፤
6. **"ህገ ወጥ ምርት"** ማለት ክልከላ የተደረገበት ወይም ገደብ ተደርጎበት የፀነ ፈቃድ ሳይሰጥበት በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ ከተደነገጉ ሥርዓቶች ውጭ በህገወጥ መልኩ የተያዘ ምርት ነው፤

7. **"ቁጥጥር የሚደረግበት ተግባር"** ማለት ክልከላ ወይም ገደብ የተደረገባቸውን ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት፣ ከሀገር የማስወጣት፣ የማምረት፣ በመገጣጠም፣ የመፍጠር፣ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የመያዝ፣ የማዘዋወር፣ ማስተዋወቅ፣ ጥቅም ላይ የማዋል እና ጥቅም ላይ እንዲውል የማመቻቸት ተግባራትን መቆጣጠርን ያጠቃልላል፤
8. **"አንድ መስኮት አገልግሎት"** ማለት ለገቢና ወጪ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን በተሟላ መልኩ በአንድ ቦታ ሁሉንም አገልግሎት ለማግኘት እንዲቻል በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘረጋ ሥርዓት ነው፤
9. **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት የአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር ነው፤
10. **"አግባብነት ያለው የሥራ ክፍል"** ማለት በአዋጁ መሠረት የተደነገጉ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ዓይነቶችን እንዲሰጥ እና የክትትልና ቁጥጥር ሥራ እንዲያከናውን ኃላፊነት የተሰጠው የአስተዳደሩ አደረጃጀት ነው፤
11. **"ኮሚቴ"** ማለት በአዋጁና በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ዙሪያ ቅር የተሰኘ ሰው የሚያቀርባቸውን ቅሬታዎች አጣርቶ ለዋና ዳይሬክተሩ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፤
12. **"ተቆጣጣሪ"** ማለት በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተዘረጋ ሥርዓት መሠረት ምርቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግ የተሰየመ የአስተዳደሩ ሠራተኛ ነው፤
13. **"አስተዳደር"** ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ነው፤
14. **"ክልል"** ማለት ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተውን ማንኛውንም ክልል፤ ወይም በህገ መንግሥቱ መሠረት የተቋቋመ ክልል እንዲሁም የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፡፡
15. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በህግ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
16. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ክልከላ ወይም ገደብ ስለተጣለባቸው ምርቶች

## 3) ክልከላ የተጣለባቸው ምርቶች

1. በሀገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ሊያደርሱ ከሚችሉት ስጋት አንፃር ክልከላ የተጣለባቸው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች በዚህ መመሪያ አባሪ 1 መሠረት ተለይተው ተሰይመዋል፤
2. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ክልከላ በተጣለባቸው ምርቶች አማካኝነት ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት አከናውኖ ከተገኘ በአዋጁ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 4) ክልከላ ለተጣለባቸው ምርቶች ስለሚሰጥ ልዩ ፈቃድ

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም አስተዳደሩ ለትምህርት ወይም ጥናትና ምርምር ዓላማ ክልከላ የተደረገበት ምርት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ፣

ከሀገር እንዲወጣ ወይም በሀገር ውስጥ እንዲመረት፣ እንዲገጣጠም እና እንዲፈጠር በዚህ አንቀፅ መሠረት በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በልዩ ሁኔታ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፡-

   ሀ/ ስለምርቱ አጠቃቀም ህጋዊ እውቅና ካለው የትምህርት፣ የጥናትና ምርምር ወይም መንግሥታዊ ተቋም ዋስትና እና የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል፤

   ለ/ በአስተዳደሩ የሚደረገውን የግለሰብ የደህንነት ማረጋገጫ መስፈርት ማሟላት የሚችል፤

   ሐ/ ስለምርቱ እና ጥቅም ላይ ስለሚውልበት አግባብ ዝርዝር መግለጫና ዕቅድ ማቅረብ የሚችል፤

   መ/ ምርቱ በሀገር ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ ለመቆጣጠር፣ ሚስጥራዊነትን ለመጠበቅና እና ተደራሽነቱን ለመወሰን  የሚዘረጋቸውን ስርዓቶች ማቅረብ የሚችል፤

   ሠ/ ምርቱን ለታሰበለትና ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ ልዩ ፈቃድ ለተሰጠው አካል ብቻ እንደሚውል ማረጋገጫ መስጠትና አስተዳደሩ በሚያዘጋጀው ቅፅ መሠረት ስምምነት መፈረም የሚችል መሆኑ እና

   ረ/ ምርቱ ለሀገር እንዲሁም ለምርምርና ፈጠራ የሚኖረው አዎንታዊ ጠቀሜታ ማሳየት የሚችል።

3. አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን እና አመልካቹ በሀገር ደህንነት ላይ የሚያደርሰው ስጋት አነስተኛ መሆኑን ሲያረጋግጥ ልዩ ፈቃዱን ማመልከቻው በቀረበ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ይሰጣል።

4. አስተዳደሩ በዚህ መመሪያ መሠረት በልዩ ሁኔታ ፈቃድ የተሰጠባቸው ምርቶች ለተፈለጉለት ዓላማ ብቻ መዋላቸው አካላዊ እና በርቀት ክትትል ማድረጊያ ዘዴዎችን በመዘርጋት በማንኛውም ጊዜ በጥብቅ ይከታተላል።

## 5) ገደብ ስለተጣለባቸው ምርቶች

1. በሀገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ላይ ሊያደርሱ ከሚችሉት የደህንነት ስጋት መነሻነት ከአስተዳደሩ በሚሰጥ የደህንነት ማረጋገጫ በፈቃድ ብቻ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ገደብ የተጣለባቸው ምርቶች በዚህ መመሪያ አባሪ 2 መሠረት ተለይተው ተሰይመዋል፤

2. ማንኛውም ሰው ከአስተዳደሩ የተሰጠ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ገደብ በተጣለባቸው ምርቶች ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት ያከናወነ እንደሆነ በአዋጁ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

## 6) ክልከላና ገደብ የተጣለባቸው ምርቶችን ዝርዝር ስለማሻሻል፤

1. አስተዳደሩ በዚህ መመሪያ መሠረት ክልከላ እና ገደብ የተጣለባቸውን ምርቶች ዝርዝር በዓመት አንድ ጊዜ በመገምገም ተገቢውን ማሻሻያ ያደርጋል፤

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚደረገው ግምገማ፡-

   ሀ/ የቴክኖሎጂ ዕድገትንና ለውጦችን፤

ለ/ ቴክኖሎጂዎቹ ከሚፈጥሩትን የስጋት ደረጃ፤
ሐ/ ወቅታዊ ዓለም አቀፋዊ አዝማሚያዎችን፤ እንዲሁም
መ/ የሀገሪቱን ቴክኖሎጂዎቹን የመቆጣጠር አቅም፤
ሠ/ ሊፈጠሩ የሚችሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን፤

ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

3. በዚህ አንቀፅ መሠረት ክልከላና ገድብ የተደረገባቸውን ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር ሲያሻሽል አሳማኝ ሳይንሣዊ ማስረጃዎችን ላይ የመመስረት፣ ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነትን ታሳቢ የማድረግ እንዲሁም የሚመለከታቸውን አካላት ማማከርና ማሳወቅ ይኖርበታል።
4. አስተዳደሩ በሚያደርገው ግምገማ መሠረት ምርቶቹ ባሉበት ደረጃ እንዲቀጥሉ፤ ከክልከላ ወይም ገደብ ዝርዝር ውስጥ እንዲወጡ ወይም የቁጥጥር ደረጃቸውን በማሻሻል ሊወስን ይችላል።

## 7) አዲስ ወይም ክሱት ምርቶችን ስለመሰየም

1. አስተዳደሩ በሀገር ደህንነት ላይ ስጋት የሚፈጥሩ አዳዲስ ወይም ክሱት ምርቶች መፈጠራቸውን ወይም መኖራቸውን ሲያረጋግጥ በማንኛውም ጊዜ ክልከላ ወይም ገደብ የተደረገባቸውን ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር በማሻሻል በመመሪያው ውስጥ ተካተው እንዲሰየሙ ሊያደርግ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ቢኖርም አዲስ ወይም ክሱት ምርቶች ሆነው የደህንነት ስጋት ደረጃቸው ያልተለየ ምርቶች ወደ ሀገር ሲገቡ፣ ከሀገር ሲወጡ እንዲሁም በተለያየ መልኩ ጥቅም ላይ ውለው ሲገኙ አስተዳደሩ የቴክኖሎጂው የስጋት ደረጃ ተገምግሞ እስኪወሰን ድረስ ምርቱን በጊዜያዊነት ሊረከብ ይችላል፤
3. አስተዳደሩ በጊዜያዊነት የተረከበውን ምርት በ30 /ሠላሳ/ የስራ ቀናት ውስጥ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 3 እና 4 መሠረት ገምግሞ ውጤቱን ለተገልጋዩ ማሳወቅ ይኖርበታል፤
4. በግምገማ ውጤቱ መሠረት ምርቱ እንደሚኖረው የደህንነት ስጋት ደረጃ አስተዳደሩ፡-

ሀ/ ለባለቤቱ ወይም ለባለይዞታው ካለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲመለስ፤
ለ/ ክልከላ በመጣል ባለቤቱ ወይም ባለይዞታው ምርቱን ወደመጣበት ሀገር እንዲመልስ ወይም ለአስተዳደሩ እንዲያስረክብ፤ ወይም
ሐ/ ገደብ በመጣል ከአስተዳደሩ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲወጣበት

ሊወስን ይችላል።

5. አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 ለ እና ሐ መሠረት አዲስ ወይም ክሱት በሆነው ምርት ላይ ክልከላ ወይም ገደብ የሚጥል ከሆነ ክልከላ እና ገደብ የተጣበለባቸውን ምርቶች ዝርዝር በማሻሻል ምርቱ እንዲሰየም ማድረግ ይኖርበታል።

## 8) ክልከላና ገደብን ስለማሳወቅ

1. አስተዳደሩ ክልከላ ወይም ገደብ የሚደረግባቸውን ምርቶች ዝርዝር ማህበረሰቡ እንዲሁም የተለዩ ተገልጋዮች በቀላሉ ሊያገኙቸው በሚችልባቸው አግባቦች ተደራሽ በማድረግ ግልፅነትን ይፈጥራል፤

2. የተለያዩ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለማሟላት ክልላና ገደብ የሚጥልባቸውን ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር ግልፅ እና በተመጠነ መልኩ በበይነ መረብ እና በአንድ መስኮት አገልግሎት በቀላሉ ሊነበቡ እና ሊወርዱ በሚችሉበት ቅርፅ ተደራሽ ማድረግ ይኖርበታል፤

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ክልከላና ገደብ የተደረገባቸው ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር በሀገር ውስጥ እንዲሁም በውጭ ሀገር ሰፊ ተናጋሪ ባላቸው ቋንቋዎች ተርጉመው መቅረብ ይኖርባቸዋል፤

4. አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ከተቀመጠው አማራጭ በተጨማሪ የምርቶች ቁጥጥር በስፋት በሚደረግባቸው አካባቢዎች ላይ በተለያዩ የወረቀትና የስክሪን ማስታወቂያዎችን መጠቀም ይኖርበታል፤ መረጃው ተደራሽ እንዲሆንም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ይጠበቅበታል።

## ክፍል ሦስት

## ስለደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ እና ቅድመ ሁኔታዎች

### 9) ስለ ደህንነት ማረጋገጫ ፍቃድ

አስተዳደሩ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ገደብ ለተጣለባቸውን ምርቶች በአዋጁ መሠረት የተለዩ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ አይነቶችን ይሰጣል።

### 10) ወደ ሀገር ለማስገባት ስለሚሰጥ ፈቃድ

1. ማንኛውም ሰው ገደብ የተደረገበትን ምርት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከአስተዳደሩ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2. በአዋጁ አንቀፅ 7 ስር የተደነገጉት ጠቅላላ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አንቀፅ መሠረት ምርቶችን ወደ ሀገር ለማስገባት የሚያመለክት ሰው የሚከተሉትን ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርበታል፤

   ሀ. ምርቱን ወደ ሀገር የሚያስገባው ሰው ስምና ቋሚ አድራሻ፤
   ለ. የምርቱን ምንነት፣ መለያ ቁጥር፣ ሞዴል፣ የምርት ዓመት፣ ቴክኒካል አቅሞች እንዲሁም አምራቹ ምርቱን አስመልክቶ የሚሰጣቸው መግለጫዎች፤
   ሐ. ምርቱ የተመረተበትን እና የተፈጠረበት ሀገር ዝርዝር መረጃ፤፤
   መ. ምርቱ ያለበት ቦታ የሚገልፅ ሰነድ፤
   ሠ. ምርቱ ጥቅም ላይ የሚውልበት ዓላማና ቦታ መግለጫ፤
   ረ. የምርቱ የመጨረሻ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን እንዲሁም ምርቱን ለሦስተኛ ወገኖች የሚተላለፍ ከሆነ በማስተላፍ ሂደት በአዋጁ መሠረት የሚወሰዱ ቅድመ ጥንቃቄዎችን የሚያሳይ መግለጫ፤
   ሰ. የምርቱ ግዥ የተፈፀመበትን የባንክ ፍቃድ ወይም የእርዳታ ከሆነ የእርዳታ ሰርቲፍኬት (Donation certificate)፤ ወይም ሌላ ግዥ የተፈፀመበትን ዘዴ የሚያሳይ ማስረጃ ቅጂ፤

ሸ. ሌሎች በዚህ መመሪያ ገደብ እንደተጣለበት የምርት አይነት በአባሪ 2 የተዘረዘሩ ተጨማሪ መስፈርቶችን።

ቀ. በመስኩ ለመሰማራት እንዲያስችል የተሰጠ የንግድ ፈቃድ ቅጂ፤

በ. የምርቱን ግዥ ለመፈፀም የተዘጋጀ የግዥ ሰነድ ቅጂ፤

3. ገደብ የተጣለበት ምርትን ለንግድ ዓላማ በአየር መጓጓዣ፣ በመርከብ፣ በተሽከርካሪ፣ በባቡር፣ በእንስሳት ወይም በሰው ተጠቅሞ በሻንጣ ወይም በእጅ ወደ ሀገር ይዞ የሚገባ ሰው የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ከሀ እስከ በ ድረስ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፤

4. ገደብ የተጣለበት ምርትን ከንግድ ዓላማ ውጭ በአየር መጓጓዣ፣ በመርከብ፣ በተሽከርካሪ፣ በባቡር፣ በእንስሳት ወይም ሰው ተጠቅሞ በካርጎ፣ በሻንጣ ወይም በእጅ ወደ ሀገር ይዞ የሚገባ ሰው የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ከሀ እስከ ሸ ድረስ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል።

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 ከተዘረዘሩ ቅድመ ሁኔታዎች በተጨማሪ አስተዳደሩ እንደ ምርቱ የስጋት ደረጃ ምርቱን ይዞ የሚገባ ሰው ከሚመለከተው የመንግስት ወይም አግባብነት ካለው ተቋም የዋስትና እና የድጋፍ ደብዳቤ እንዲያቀርብ አስተዳደሩ ሊወስን ይችላል።

## 11) ስለቅድመ-ፈቃድ

1. ማንኛውም ሰው በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ገደብ የተጣለበትን ወይም አዲስ ወይም ክሱት ምርት ሆኖ ክልከላ ወይም ገደብ ሊጣልበት የሚችል መሆኑን ጥርጣሬ ካደረበት ለቅድመ ፈቃድ ማመልከት ይችላል፡፡

2. የቅድመ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው በአዋጁ አንቀፅ 7 ስር የተደነገጉት ጠቅላላ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 10 ከሀ እስከ ረ ድረስ ያሉ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ መቅረብ ይኖርበታል።

3. መስፈርቶችን አሟልቶ ምርቱን ወደ ሀገር እንዲያስመጣ ከአስተዳደሩ ቅድመ-ፈቃድ የተሰጠው ሰው ምርቱ ወደ ሀገር ካስገባ በኋላ በዚህ መመሪያ በተዘረጉ ሥርዓቶች መሠረት ምርቱን ወደ ሀገር ለማስገባት የሚያስችል ፈቃድ ማግኘት አለበት።

## 12) ወደ ውጭ ለመላክ ስለሚሰጥ ፈቃድ

1. ማንኛውም ሰው ገደብ የተጣለበትን ምርት ከሀገር ውጪ ለመላክ ከአስተዳደሩ ምርት ወደ ውጭ መላኪያ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2. በአዋጁ አንቀፅ 7 ስር የተደነገጉት ጠቅላላ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ገደብ የተደረገበትን ምርት ከሀገር ለማስወጣት የሚያመለክት ሰው የሚከተሉትን ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ. ምርቱን ከሀገር የሚያስወጣው ሰው ስምና ቋሚ አድራሻ፤

ለ. ከሀገር የሚወጣው ምርት ምንነት፣ መለያ ቁጥር፣ ሞዴል፣ የምርት ዓመት፣ ቴክኒካል አቅሞች እንዲሁም አምራቹ ምርቱን አስመልክቶ የሚሰጣቸው መግለጫዎች፤

ሐ. ምርቱ ከሀገር የሚወጣበት ምክንያት ወይም ዓላማ፤
መ. ምርቱ የሚላክበት ወይም የሚላክለት ሰው ሙሉ መረጃ ወይም አድራሻ፤
መ. ምርቱን አቅርቦ ማስፈተሽና ማረጋገጥ፤
ሠ. ምርቱ እንዲወጣ ፋቃድ የሚሰጥ ተቋም ካለ አግባብነት ካለው ተቋም ስልጣን ባለው አካል የተፈረመ ደብዳቤ ቅጂ፤
ረ. ምርቱ ከውጭ ሀገር አስቀድሞ የገባ ከሆነ ምርቱ ወደ ሀገር ውስጥ የገባበት ፍቃድ ቅጂ፤
ሰ. ምርቱ የሚላከው ለንግድ ዓላማ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የንግድና የላኪነት ፈቃድ ቅጂ፤
ሸ. የምርቱ የመጨረሻ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን እንዲሁም ምርቱን ለሦስተኛ ወገኖች የሚተላለፍ ከሆነ በማስተላፍ ሂደት በአዋጁ መሠረት የሚወሰዱ ቅድመ ጥንቃቄዎችን የሚያሳይ መግለጫ፤
ቀ. እንደ ሚላከው ምርት አይነት በዚህ መመሪያ አባሪ የተደረጉ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች።

## 13) ለማምረት፣ ለመገጣጠም ወይም ለመፍጠር ስለሚሰጥ ፈቃድ፤

1. ማንኛውም ሰው ገደብ የተደረገባቸውን ምርቶች በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ለመገጣጠም ወይም ለመፍጠር ከአስተዳደሩ አስቀድሞ የደህንነት ማረጋገጫ ማግኘት ይኖርበታል፤
2. በአዋጁ አንቀፅ 7 ስር የተደነገጉት ጠቅላላ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ገደብ የተደረገበትን ምርት በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ለመገጣጠም ወይም ለመፍጠር የሚያመለክት ሰው የሚከተሉትን ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ. የአመልካቹን ስምና ቋሚ አድራሻ፤
ለ. የሚመረተው፣ የሚገጣጠመው ወይም ሊፈጠር የታሰበው ምርት ምንነት፣ ሞዴል እና ቴክኒካል አቅሞች ዝርዝር መግለጫዎች፤
ሐ. ምርቱ የሚመረትበት፣ የሚገጣጠምበት ወይም የሚፈጠርበት ምክንያት፤
መ. ምርቱ የመጨረሻ ተጠቃሚ የሚሆኑ አካላት ማብራሪያ፤
ሠ. ለምርቱ ግብዓት የሚያቀርቡ የሀገር ውስጥ ወይም የውጭ ሰዎች ካሉ የሰዎቹ መግለጫ፤
ረ. ምርቱ የሚመረተው፣ የሚገጣጠመው ወይም የሚፈጠረው ለንግድ ዓላማ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የንግድና የላኪነት ፈቃድ ቅጂ፤
ሰ. የምርቱ የመጨረሻ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን እንዲሁም ምርቱን ለሦስተኛ ወገኖች የሚተላለፍ ከሆነ በማስተላፍ ሂደት በአዋጁ መሠረት የሚወሰዱ ቅድመ ጥንቃቄዎችን የሚያሳይ መግለጫ፤
ሸ. እንደ ሚፈጠረው የምርት አይነት አስተዳደሩ የሚያወጣቸው ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች።

## 14) ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት ለማከናወን ስለሚሰጥ ፈቃድ

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ 10 እስከ 13 ከተደነገጉት ውጭ ያሉ ገደብ የተደረገባቸውን ምርቶች ላይ ቁጥጥር የሚደርግባቸውን ተግባራት ለማከናወን እንደ አግባብነቱ ከአስተዳደሩ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው በአዋጁ አንቀፅ 7 ስር የተደነገጉት ጠቅላላ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ የሚከተሉትን ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፡-
   - ሀ. የአመልካቹን ስምና ቋሚ አድራሻ፤
   - ለ. የሚያከናውን ቁጥጥር የሚደረግበት የተግባር አይነት ዝርዝር፤
   - ሐ. ጥቅም ላይ ሊያውለው ያሰበውን ምርት ምንነት፣ ሞዴል፣ የስሪት ሀገር እና ቴክኒካል አቅሞች ዝርዝር መግለጫዎች፤
   - መ. ለተግባሩ ምርት ወይም አገልግሎት የሚያቀርቡ የሀገር ውስጥ ወይም የውጭ ሰዎች መግለጫ፤
   - ሠ. ተግባሩን የሚያከናውነው ለንግድ ዓላማ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የንግድና የላኪነት ፈቃድ ቅጂ፤
   - ረ. የምርቱ የመጨረሻ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን እንዲሁም ምርቱን ለሦስተኛ ወገኖች የሚተላለፍ ከሆነ በማስተላፍ ሂደት በአዋጁ መሠረት የሚወሰዱ ቅድመ ጥንቃቄዎችን የሚያሳይ መግለጫ፤
   - ሰ. እንደ ሚያከናውነው ተግባር አይነት አስተዳደሩ የሚያወጣቸው ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች።
3. በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ 10 እስከ 13 ባሉ የተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ የደህነንት ማረጋገጫ የተሰጠው ሰው ካለተጨማሪ ፈቃድ ምርቶችን የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማስተዋወቅ እና ጥቅም ላይ የማዋል መብት ይኖረዋል፤
4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ቢኖርም ፈቃድ የተሰጠው ሰው ምርቶችን ያስተላለፈላቸውን የመጨረሻ ተጠቃሚዎች በአዋጁ በተደነገገው ግዴታ መሠረት ለአስተዳደሩ ማሳወቅ እና ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል።

# ክፍል ሦስት
# ስለፈቃድ አሰጣጥ እና ዕድሳት

## 15) ማመልከቻ ስለማቅረብ

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት የተደነገገ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ዓይነቶችን ለማግኘት አስተዳደሩ የሚያዘጋጀው መደበኛ ቅፅ በመሙላት በራሱ ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ማመልከቻውን ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም አግባብነት ላለው የሥራ ክፍል ማቅረብ ይኖርበታል፤

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ እንደ አግባብነቱ በአንድ መስኮት አገልግሎት፣ አስተዳደሩ በሚያመቻቸው የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ወይም በአካል መቅረብ ይኖርበታል፤

3. በዚህ አንቀፅ መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ የደህንነት ፈቃዱን ለማግኘት ከተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን ከሚያረጋግጡ ደጋፊ ሰነዶች ጋር ተሟልተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፤

## 16) ማመልከቻ ስለማቅረቢያ ጊዜ

በዚህ መመሪያ መሠረት የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ:-

1. ገደብ የተደረገበትን ምርት ወደሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ምርቱ ወደ ሀገር እንደገባ ወዲያውኑ ማመልከቻውን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. ቅድመ-ፈቃድ ደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ማመልከቻውን ምርቱ ከመጫኑ በፊት በማንኛውም ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. ገደብ የተደረገበትን ምርት ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ምርቱ ለመጫን ከታሰበበት ቀን ቢያንስ 15 ቀን አስቀድሞ ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ማከልከቻው ከቱሪስት የሚቀርብ ከሆነ ከመሄዱ ቢያንስ ከአንድ ቀን በፊት በቱሪስቱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት ማሳወቅ ይኖርበታል፤
4. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13 ወይም 14 ላይ የተዘረዘሩ የደንነነት ማረጋደገጫ ፈቃድ ዓይነቶች መካከል አንዱን ለማግኘት የሚፈል ሰው ተግባሩን ለማከናወን ካሰበበት ቢያንስ 15 ቀናት ቀድም ብሎ ባሉ የሥራ ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 17) ምላሽ ስለመስጠት

አስተዳደሩ:-

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በመመርመር ቢበዛ 10 ቀናት ጊዜ ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፤
2. የቀረበው ማመልከቻው የተሟላ እና የሚጠየቁ መስፈርቶች ተሟልተው የቀረቡ እንደሆነ አስተዳደሩ ተገቢውን ግምገማና የማጣራት ሂደት ተከትሎ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃዱን ይሰጣል፤
3. የቀረበው ማመልከቻ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መረጃውን ተሟልቶ እንዲቀርብ ለአመልካቹ ይመለስለታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መረጃውን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፤ በዚህ አግባብ ጥያቄው የተሰረዘበት ሰው በድጋሚ በአዲስ መልክ የማመልከቻ ክፍያ በመፈፀም ማመልከት ይችላል፤

## 18) ስምምነት ስለመግባት

1. አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃድ እንደሚሰጥበት የምርት ዓይነት አጠቃቀምን እና ያሉ ገደቦች አስመልክቶ ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ አስገዳጅ ስምምነት ቅፅ አዘጋጅቶ አመልካች እንዲፈርም ያደርጋል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት አመልካች የሚፈርመው የስምምነት ቅፅ እንደ አግባብነቱ ፈቃዱ በሚታደስበት ወቅት በየዓመቱ መታደስ ይኖርበታል።

## 19) ፈቃድ ስለማደስ

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠው ፈቃድ ከጊዜ ገደብ ጋር የተሰጠው ከሆነ በፈቃዱ ላይ ያለው የጊዜ ገደቡ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ለአስተዳደሩ የፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ አስተዳደሩ በሚያመቻቸው ኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ወይም በአካል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚያቀርበው የፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ የሚከተሉትን ቅደመ ሁኔታዎች ተሟልተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡

    ሀ. ከአስተዳደሩ አስቀድሞ የተሰጠ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ፤
    ለ. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቱ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፤
    ሐ. ፈቃዱ ሲሰጥ የተጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች አለመጓደላቸውን የሚያሳይ አጭር መግለጫ፤ እና
    መ. ከአስተዳደሩ ጋር የተገባ የግዴታ ስምምነት ሰነድ፤

3. አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ መሠረት የሚቀርብለት ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄና አስፈላጊ ሰነዶችን መርምሮ እና ምርቱ ላይ ተገቢውን ግምገማ በማድረግ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፤
4. በዚህ አንቀፅ መሠረት አስተዳደሩ በሚያደርገው ግምገማ ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ከቀረቡ ፈቃዱን ያድሳል፤ መስፈርቶቹ ካልተሟሉ ፈቃዱን ይሰርዛል ምርቱንም በዚህ መመሪያ በተዘረጋው ስርዓት መሠረት ሊወርስ ይችላል።

## 20) ፈቃድ የሚሰረዝባቸው ሁኔታዎች

በአዋጁ አንቀፅ 11 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምርቱን በሚመለከት ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃዱ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፤

1. ምርቱን በሚመለከት ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ ለአስተዳደሩ ሳያሳውቁ ምርቱ ላይ ማንኛውም አይነት ማሻሻያ ወይም ለውጥ ሲደረግ፤
2. ምርቱ በሚመለከት ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ ምርቱ ላይ የህግ ጥያቄ ወይም ክርክር ተነስቶ በፍርድቤት የእግድ ትዕዛዝ ሲሰጥ፤
3. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቱ በሚመለከት ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ ምርቱ በሀገር ላይ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን ሲረጋገጥ፤

# ክፍል አራት
# ስለክትትልና ቁጥጥር

## 21) ክትትል እና መረጃ አያያዝ

አግባብነት ያለው የስራ ክፍል ፈቃድ የተሰጣቸውን ሰዎችን መረጃ ያደራጃል፣ በተሰጣቸው ፈቃድ፣ በገቡት ስምምነትና በአዋጁ መሠረት እየሠሩ ስለመሆኑ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፡፡

## 22) ተቆጣጣሪ ስለሚሰየምባቸው መስፈርቶች፣

1. አስተዳደሩ በአዋጁ አንቀፅ 15 መሠረት የሚሰይማቸው ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟሉ መሆን ይገባቸዋል፡
   - ሀ. ምርቶች ላይ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል በቂ የሆነ የትምህርት ዝግጅትና እውቀት ያለው፤
   - ለ. ምርቶች ሊፈጥሩ ስለሚችሉት ስጋትና ተጋላጭነቶችን ለመለየት የሚያስችል አቅም ያለው፤
   - ሐ. አግባብነት ያላቸውን የደህንነት ማረጋገጫ እና የሀገሪቱ ህጎችና የአሰራር ስርዓቶች ላይ በቂ እውቀት ያለው፤
   - መ. ምርቶች ለመቆጣጠር እና ለመመርመር የሚያስችሉ ስነ ዘዴዎች እና መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ በቂ ልምድ ያለው፤
   - ሠ. በአዲስ መልክ እየተሻሻሉ በመጡ እና መፃዒ ቴክኖሎጂዎች ላይ ራሱን ዝግጁ የሚያደርግና በቀጣይነት ራሱን የሚያበቃ፤
   - ረ. ጠንካራ የትንታኔ እና የችግር አፈታት ችሎታዎች ያሉት፤
   - ሰ. ውጤታማ የተግባቦት አቅም እና ከባለድርሻዎች ጋር በቅንጅት የመስራት የሚችል፤
   - ሸ. ስራውን በገለልተኝነት፣ በታማኝነት እና ሙያዊ ሥነ-ምግባሩን በጠበቀ መልኩ ሊሰራ የሚችል እና ለሥራው አሉታዊ የሆኑ ተፅዕኖዎች የሌሉበት፤
   - ቀ. ሚስጥር የመጠበቅ አቅም ያለውና ከስራው ጋር የጥቅም ግጭት የሌለበት፤
   - በ. የተሻለ የስራ አፈፃፀም ያለው እና ምንም አይነት የዲሲፕሊን ጥፋት ሪከርድ የሌለበት፤
2. አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተቆጣጣሪዎችን ለመሰየም ደረጃቸውን የጠበቁ መመዘኛ እና የግለሰብ ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓቶችን ይዘረጋል፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የተቀመጡ መመዘኛዎቸንና የደህንነት ማረጋገጫ ያሟሉ የአስተዳደሩ ሰራተኞች ብቻ በተቆጣጣሪ ባለሙያነት ይሰየማሉ።
4. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰየሙ ባለሙያዎች ከአስተዳደሩ ምንነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ ሊሰጣቸው ይገባል፤ መታወቂያው የሚከተሉት ይዘቶች ሊኖሩት ይገባል፡-
   - ሀ. የተቆጣጣሪ ባለሙያውን ሙሉ ስም፤
   - ለ. በቅርብ ጊዜ የተነሳው ፎቶግራፍ፤
   - ሐ. የአስተዳደሩን ስም እና መለያ ሎጎ፤

መ. የግለሰቡን ልዩ መለያ ቁጥር፤
ሠ. መታወቂው የተቆጣጣሪ መሆኑን በግልፅ በሚታይ መልኩ ማሳየት
ረ. ተቆጣጣሪው የስራ ስያሜ እና ደረጃ፤
ሰ. መታወቂያው የተሰጠበትና የሚያበቃበትን ቀን፤
ሸ. የአስተዳደሩን መገኛ አድራሻ
ቀ. የሚመለከተው ሥራ ክፍል ኃላፊ ፊርማ።

## 23) የተቆጣጣሪዎች ሙያዊ የስነምግባር ግዴታዎች

ተቆጣጣሪ የሚከተሉት የሙያ ሥነ-ምግባር ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

1. ተግባሩን በሚያከናውንበት ወቅት የሚያገኛቸውን የአመልካቾች የግል መረጃዎች፣ የንግድ ሚስጥሮች፣ የስራ መረጃዎችን እንዲሁም ማንኛውንም ዓይነት የተሰበሰቡ መረጃዎች በጥብቅ ሚስጥርነት የመያዝ፤
2. ተግባሩን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ብቻ የመሰብሰብ፤ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በአግባቡ ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ የማስቀመጥ ወይም እንደ አግባብነቱ የማስወገድ፤
3. በተሰጠው ስልጣንና ተግባር ወሰን ብቻ በአዋጁ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን ተከትሎ ፍተሻና ምርመራ የማድረግ፤
4. ለሁሉም የቁጥጥር ስራዎች ተመሳሳይ የሆኑ የወጡ ደረጃዎችና መስፈርቶችን በመጠቀም የመፈተሽና የመቆጣጠር፤ ሂደቶቹን ቁጥጥር ለሚደረግባቸው አካላት የማሳወቅና ግለፅነት የመፍጠር፤
5. ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ እና ፕሮቶኮሉን ጠብቆ የመገኘት፤
6. የስራ ላይ የደህንነት እና ጤና እርምጃዎችን የመከተል፤
7. የስራ ሪፖርቶችን በተጨባጭ ማስረጃ ላይ የተመሰረቱ፣ ትክክለኛ፣ ታማኝ እንዲሆኑ ማድረግ እና ግላዊ ፍላጎትን ከሚያንፀባርቁ ትርጓሜዎችን ወይም አሳሳች መረጃዎችን የማስወገድ፤
8. የፍተሻ ተግባሩን ከግላዊ ፍላጎቶችና አስተያየቶች፣ ከጥላቻ እንዲሁም ከማንኛውም ውጫው ተፅዕኖ ውጭ ሆኖ በገለልተኝነት የማከናወን፤
9. የጥቅም ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ ፍተሻ ላይ ከመሳተፍ መቆጠብ እና ግጭት ሊፈጠር የሚችለውን ጉዳይ አግባብነት ላለው የስራ ክፍል ኃላፊ ወዲያውኑ ማሳወቅ፤
10. ከቁጥጥር ስራው ጋር ተያይዞ ጉቦ፣ ስጦታ ወይም ማንኛውንም ዓይነት መደለያ ከመቀበል ተቆጠብ
11. ከቴክኖሎጂ ቁጥጥር ጋር የተዛመደ የስነምግባር ጉድለት ካስተዋለ ወይም ከጠረጠረ ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፤
12. በምርመራ ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ሰዎች ሁሉ በአክብሮት እና ትህትና የማስተናገድ፤
13. ከስራ ባልደረቦች፣ ከባለድርሻ አካት እንዲሁም ከተገልጋዮች ጋር በትብብርና በቅንጅት የመስራት፤ የባህል ልዩነቶችን ማክበር እና የግንኙነት ዘይቤዎችን በዚህ መሠረት ማስተካከል፤
14. በቴክኖሎጂ ቁጥጥር ሙያ መስክ ላይ እውቀትን ለመጠበቅ ሙያዊ እድገት እድሎችን በመደበኛነት መጠቀምና ሁልጊዜ የመማር፤

ረቂቅ

15. እውቀትን እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ከስራ ባልደረቦች ጋር በማካፈል ለሙያው እድገት አስተዋጽዖ ማድረግ፤
16. በአዋጁና በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ግዴታዎችን የማክበር።

## 24) ስለተቆጣጣሪ ስለመደብና ቁጥጥር ስለማድረግ፤

1. አግባብነት ያለው የሥራ ክፍል በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት የተመለመሉ ተቆጣጣሪዎችን አስፈላጊነታቸው በታመነባቸው የጉምሩክ ጣቢያዎች ሁሉ ላይ እንዲሁም በአስተዳደሩ ቢሮዎች ላይ ይመድባል፤
2. ምደባ የተደረገላቸው ተቆጣጣሪዎች በተመደቡበት የጉምሩክ ጣቢያዎች ላይ በሳምንት ሰባት ቀን ለሃያ አራት ሰዓት በፈረቃ በመገኘት የቁጥጥር ተግባራቸውን የሚያከናውኑ ይሆናል፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እነደተጠበቀ ሆኖ፤ አግባብነት ያለው የሥራ ክፍል በሚዘረጋው ስርዓት መሠረት በየወቅቱ በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በመንቀሳቀስ ፈቃድ የተሰጣቸውን ሰዎች እንዲሁም በህገ ወጥ መልኩ ምርቶች ጥቅም የሚውሉባቸውን ቦታዎች በመለየት ቁጥጥር የሚያደርጉ ተቆጣጣሪዎችን ያሰማራል፤ ኦፕሬሽኖችን ይሰራል፤
4. ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት ምርቶቹ የተያዙበት፣ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ወይም የተቀመጡበት ቦታ የደህንነት ስጋትን የሚፈጥር ሆኖ ካገኘው፤ እንደ አግባብነቱ ከመከላከያ ሠራዊት፣ ፌዴራል ፖሊስ ወይም ክልል ፖሊስ ሃይሎት ጋር በጋራ ኦፕሬሽኑን ይሰራል።

## 25) ስለተቆጣጣሪዎች ስራ ከባቢና ፕሮቶኮል

አስተዳደሩ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የቁጥጥር ስራ ለሚሰሩ የስራ ክፍሉ ሰራተኞች

1. ተቆጣጣሪዎች ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ምቹ ከባቢ ሁኔታ በተለያዩ የጉሙሩክ ጣቢያዎች በሚኖሩ ቢሮዎች እንዲኖር ያደርጋል፤
2. አስተዳደሩ ተቆጣጣሪዎች የቁጥጥር ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል አጋዥ የሆኑ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች፣ የመጠይቅ ክፍሎችን፣ በተለያዩ የጉሙሩክ ጣቢያዎች በሚኖሩ ቢሮዎች እንዲኖር ያደርጋል፤
3. አስተዳደሩ አስፈላጊ የሆኑ እና የተሟላ የደህንነት እና ጤንነት ማስጠበቂያ ቁሳቁሶችን ያሟላል፤
4. ሰራተኞቹ በመደበኛነት ከሚሰሩበት ቦታ ውጭ በሚገኙ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ላይ እንዲሰሩ የሚመደቡ ከሆነ አስፈላጊውን የምግብ እና መጠጥ አገልግሎት በአስተዳደሩ ስታንዳርድ መሠረት እንዲያገኙ ያደርጋል፤
5. ተቆጣጣሪዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ተመሳሳይ የሆኑ አልባሳት ፕሮቶኮሉን በጠበቀ መልኩ እንዲጠቀሙ ይደረጋል።

## 26) ምርቶች ስለማስቀመጥ፤

1. ተቆጣጣሪው በሚያደርገው ቁጥጥር ከህግ እና ከፍቃድ ውጭ ጥቅም ላይ የዋሉ ምርቶችን ሲይዝ ለምርቶቹ ተገቢውን ምዝገባ በማድረግ፤ እንዲወረሱና አስተዳደሩ ባመቻቸው ቦታ ላይ ተገቢውን ሙያዊ ጥንቃቄ በማድረግ ያስቀምጣል፤
2. ህገ ወጥ ምርቱ ወደ ሀገር ሲገባ ወይም ከሀገር ሲወጣ በጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የተያዘ ከሆነ ለምርቱ ተገቢውን ምዝገባ በማድረግ እንዲወረስና የደህንነት ስጋት በማይፈጥር መልኩ በጉምሩክ መጋዘን እንዲቀመጥ ይደረጋል፤
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ቢኖርም የተያዘው ምርት በጉምሩክ መጋዘኖች መቀመጡ ለሀገር ደህንነት ስጋት የሚፈጥር መሆኑ በባለሙያዎች ከተረጋገጠ ምርቱ በአስተደደሩ በሚያዘጋጀው መጋዘን እንዲቀመጥ ይደረጋል፤
4. አስተዳደሩ በዚህ አንቀፅ መሠረት በሚደረጉ የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት የሚያዙ ምርቶች የሚቀመጡበት ደረጃውን እና ደህንነቱ የተጠበቀ መጋዘን ያዘጋጃል፤
5. በዚህ አንቀፅ መሠረት የሚዘጋጀው መጋዘን አካላዊ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተገቢው የሆኑ የሙቀትና ቅዝቃዜ መቆጣጠሪያ ያለው፣ ለገመድ አልባ ምርቶች የሚሆን የኔትወርክ መገደቢያ ቴክኖሎጂዎችን የያዘ እንዲሁም የሚያዙ ምርቶች ላይ ማንኛቸውን አይነት የደህንነት ስጋት በማይፈጥር ሁኔታ ደረጃውን ጠብቆ የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል፤
6. በሚደረግ ቁጥጥር መሠረት የሚያዙ ምርቶች ከተያዙበት ጊዜ ጀምሮ ያላቸው እያንዳንዱ እንቅስቃሴ እና ለውጦች ዑደት ተመዝግቦ በዝርዝር የአያያዝ ሰንሰለት ሰነድ መሰነድ ይኖርበታል።

## 27) ምርቶች ጥቅም ላይ ስለማዋል

1. በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ተይዘው የተወረሱ ምርቶችን ለደህንነት ስጋት በማይፈጥሩበት መልኩ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይቻላሉ፤
2. አስተዳደሩ እንደተወረሱ ምርቶች አይነት እና ባህሪ ተገቢውን የደህንነት ፍተሻና ግምገማ በማድረግ እንደ አግባብነቱ ከተልዕኳቸው ጋር ተጣጣሚ ለሆኑ የፀጥታና ደህንነት ተቋማት፣ የመንግሥት ተቋማት እንዲሁም ለትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተደራሽ በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይችላል፤
3. ምርቶች ለተለያየ ጥቅም በዚህ አንቀፀ መሠረት ከመዋላቸው በፊት አስቀድሞ የተሟላ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ በሚመለከት የስራ ክፍል በኩል ለአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር ቀርቦ መፅደቅ ይኖርበታል።
4. በዚህ አንቀፅ መሠረት ምርቶቹ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት አስተዳደሩ ምርቶቹ ውስጥ ያሉ መረጃዎችን ደህንነቱ በተጠበቀ ሶፍትዌር መፅዳትና መጥፋት፣ ተጋላጭነታቸውን በመፈተሽ ተቢውን ማሻሻያ ማድረግ እንዲሁም አስፈላጊውን ሁሉ የደህንነት ጥንቃቄ መውሰድ ይኖርበታል፤
5. በዚህ አንቀፅ መሠረት ምርቶቹ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት ምርቶቹን አስመልክቶ የተጀመረ አስተዳደራዊ ቅሬታ ወይም የፍርድ ቤት ሂደት ካለ መጠናቀቁ ወይም ጉዳዩ ወደፊት ጥያቄ ሊያስነሳ የማይችልና የተዘጋ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል።

## 28) ምርቶች ስለሚወገዱበት አግባብ

1. አስተዳደሩ በአዋጁና በዚህ አንቀፅ መሠረት ተወርሰው በመጋዘን የተቀመጠ ምርት፡-

    ሀ. በብልሽት ወይም በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ ከተረጋገጠ፤

    ለ. ባለበት ተጋላጭነት ምክንያት ለሌላ ጥቅም የማይውል ከሆነ፤

    ሐ. ጥቅም ላይ ቢውል የደህንነት ስጋት የሚያስከትል ከሆነ፤ ወይም

    መ. በሚደረግ ፍተሻ ምርቱ ጥቅም ላይ የማይውልና ምንም ዓይነት እሴት የማይጨምር ከሆነ፤

   በቋሚነት እንዲወገድ ያደርጋል።

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 በተደነገገው መሠረት ምርቱ ከመወገዱ በፊት ለምርቱ መወገዱ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች እና ሌሎች አማራጮች አለመኖራቸው ማረጋገጫ በሪፖርት እና የውሳኔ ሃሳብ ለዋና ዳይሬክተሩ መቅረብና መፀደቅ ይኖርበታል።
3. እንዲወገድ የተሰነ ምርት ዙሪያ ቅሬታ ከቀረበበት ጉዳዩን ለኮሚቴ ቀርቦ እንደገና እንዲመረመር ያደርጋል፡፡
4. ምርቶች ከመወገዳቸው በፊት ምርቶቹን አስመልክቶ የተጀመረ አስተዳደራዊ ቅሬታ ወይም የፍርድ ቤት ሂደት ካለ መጠናቀቁ ወይም ጉዳዩ ወደፊት ጥያቄ ሊያስነሳ የማይችል እና የተዘጋ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፤
5. ምርቱ ከመወገዱ በፊት አስፈላጊ መስፈርቶችን በሚያሟሉ ሶፍትዌሮች ምርቱ የያዘው መረጃ ወይም ውሂብ በቋሚነት እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲፀዳ እንዲሁም አገልግሎት እንዳይሰጥ መደረግ ይኖርበታል፤
6. በዚህ አንቀፅ መሠረት ምርቱ አካባቢን በማይበክል እና የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓቶችን በጠበቀ መልኩ አንደአግባብነቱ በመፍጨት፣ በመቅበር፣ በማወላለቅ፣ በማቃጠል ወይም ሌላ አግባብነት ባላቸው በመንግስት በሚዘረጉ ስርዓቶች መሠረት እንዲወገድ እና መልሶ ጥቅም ላይ እንዳይውል መደረግ ይኖርበታል፤
7. ምርቱ የሚወገድበት ወቅት የሚመለከታቸው የአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊዎች ወይም ተወካዮች እንዲሁም የፖሊስ ተወካዮች ተገኝተው ሂደቱን እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡

# ክፍል አምስት
# የቅሬታ አቀራረብና አፈታት
# ሥነ-ሥርዓት

## 29) ቅሬታ ስለማቅረብ

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ቅር ከተሰኘ ቅሬታውን ለአስተዳደሩ ማቅረብ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚቀርበው የቅሬታ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

    ሀ. የቅሬታ አቅራቢው ስምና አድራሻ፤

    ለ. የቅሬታው ምክንያት፣

    ሐ. ማህተም ወይም ፊርማ ያረፋቸውን ደጋፊ ሰነዶች

መ. የሚፈለገው መፍትሔ፤
ሰ. ቀን፣ ፊርማና ማኅተም

## 30) ቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜና ቦታ

1. ማንኛውም ቅሬታ የሚያቀርብ ሰው የቅሬታው መንስዔ የሆነው ጉዳይ ከተከሰተ ጀምሮ ባሉ አስር የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ውሳኔውን ለሰጠው አግባብነት ላለው የሥራ ክፍል ማቅረብ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የቅሬታ ማመልከቻ ለማቅረብ ካልቻለ ቅሬታ ያላቀረበበትን ምክንያት ለአስተዳደሩ አቅርቦ ምክንያቱ ተቀባይነት ሲያገኝ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን እንዲያቀርብ ይደረጋል፤
3. አመልካቹ ቅሬታውን እንደአግባብነቱ በአስተዳደሩ ዋና መስሪያ ቤት፣ ቦሌ በሚገኘው ቅርንጫፍ ፅሕፈት ቤት ወይም በክልል በተከፈቱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በአካል ወይም በአስተደዳደሩ በሚያቀርበው የኤሌክትሮኒክስ ቅሬታ የማቅረቢያ ዘዴ ሊያቀርብ ይችላል።
4. ለቅሬታ መንስዔው መነሻ የሆነውን ውሳኔ የወሰነው አግባብነት ያለው የሥራ ክፍል የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሹን መስጠት ይኖርበታል።
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት በሚሰጠው ምላሽ ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን በፅሁፍ ውሳኔው በደረሰው አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር ማቅረብ ይችላል።

## 31) ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ስለማቋቋም

በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ዙሪያ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አጣርቶ ለዋና ዳይሬክተሩ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ መሠረት ተቋቁሟል።

## 32) የኮሚቴው አባላት

1. ኮሚቴው አምስት አባላት ይኖሩታል፡፡
2. የኮሚቴው ሰብሳቢና ፀሐፊ በዋና ዳይሬክተር ይሰየማሉ፡፡
3. የኮሚቴው ሶስት አባላት በዘርፉ ተገቢው ሙያ በቂ ልምድ ካላቸው ባለሙያዎች ተውጣጥተው በሚመለከታቸው ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ይሰየማሉ፤
4. የኮሚቴው አባላት የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡ የአገልግሎት ዘመኑ እንዳግባብነቱ ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ ሊራዝም ይችላል፤

## 33) የኮሚቴው ስብሰባ

1. ኮሚቴው ለሥራ ባስፈለገ መጠን በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤
2. በስብሰባው ላይ ሰብሳቢውና ሁለት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

3. የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ የሚያልፈው በድምጽ ብልጫ ነው፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ያቀረበው ሀሳብ ያልፋል፡፡ በሃሳብ የተለየው አባል የተለየበትን ምክንያት በግልጽ እንዲሰፍር ያደርጋል፤
4. ኮሚቴው የራሱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 34) አባልነት ስለመሰረዝና ከስብሰባ ስለመነሳት

1. ማንኛውም የቅሬታ ኮሚቴ አባል አቤቱታ ካቀረበው ሰው ጋር ፀብ ወይም የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ወይም የጥቅም ግጭት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ለተያዘው ጉዳይ ብቻ ከስብሰባው ይነሳል፡፡
2. ማንኛውም የኮሚቴ አባል፡-

   ሀ. በኮሚቴው በመታየት ላይ ያለውን ጉዳይ በሚመለከት ሚስጥር ካባከነ፤ ወይም
   ለ. የኮሚቴውን ሥራ በማንኛውም አኳኋን ካስተጓጎለ
   ሐ. የሚጠበቅበትን ሙያዊ ስነ ምግባር ካጓደለ፤

   ከአባልነት ይሰረዛል፡፡

## 35) ቅሬታን ስለማጣራት

1. ኮሚቴው የቅሬታ ማመልከቻ ሲቀርብለት በአንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ (2) የተዘረዘሩ መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ ይቀበላል፡፡
2. ኮሚቴው፡-

   ሀ. የቅሬታ ማመልከቻውንና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች ይመረምራል፤
   ለ. ቅሬታ በቀረበት ጉዳይ ላይ አንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከታቸው አካላት ማብራሪያ ይጠይቃል፤
   ሐ. አግባብ የሆኑ ሕጎችንና የአሰራር ሥርዓቶችን በማገናዘብ ያጣራል፡፡

3. ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ በማጣራት ሂደት ተጨማሪ ማስረጃና ማብራሪያ አንደአስፈላጊነቱ እንዲያቀርብ በኮሚቴው ሊጠየቅ ይችላል፤
4. የቅሬታ ኮሚቴው የሚያጣራውን ውጤትና የውሳኔ ሃሳብ የያዘ ሪፖርት ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር የሥራ ቀናት ውስጥ ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፡፡

## 36) ውሳኔ ስለመስጠት

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በደረሰው በአስራ የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሀሳቡን መርምሮ ያፀድቃል፤
2. የውሳኔው ሀሳብ አሳማኝ ሳይሆን ሲቀር ኮሚቴው ጉዳዩን በድጋሚ እንዲያየው ሊያደርግ ይችላል፤
3. በዚህ አንቀፅ መሠረት የዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ አቅራቢው በፅሑፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፤
4. ቅሬታ አቅራቢው በሚደርሰው የዋና ዳይሬክተሩ ውሳኔ ካልረካ ቅሬታውን አግባብነት ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

## 37) መረጃ ስለመጠየቅና መቀበል

1. ቅሬታ አቅራቢው በዚህ መመሪያ መሠረት ኮሚቴው ለሚያከናውናቸው ተግባራት አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው፤
2. በዚህ አንቀፅ 1 መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ማንኛውም አካል የተጠየቁትን መረጃዎች የመስጠትና የማቅረብ ግዴታ አለበት።

# ክፍል ስድስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 38) ተጠያቂነት

በአዋጁ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የተደነገገውን በመተላለፍ ለራሱ ወይም ለሶስተኛ ወገን ጥቅም ለማስገኘት ሲል ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ የተጣለበትን ሙያዊ ግዴታ እና ኃላፊነት በአግባቡ ያልተወጣ ተቆጣጣሪ፣ የኮሚቴ አባል ወይም የአስተዳደሩ ሠራተኛ በዲሲፕሊን እንዲሁም እንደአግባብነቱ በፍትሐብሔር ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

## 39) ስለመመሪያው መሻሻል

አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል።

## 40) የስራ ማንዋል እና ኮታሎግ ስለማውጣት

የአስተዳደሩ አግባብነት ያለው የሥራ ክፍል ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም ዝርዝር የሆነ የስራ ቴክኒካል ማንዋል እና ምርቶችን የሚቆጣጠርበት ዝርዝር ካታሎግ ያወጣል፡፡

## 41) ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1. የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የቴክኖሎጂ ደህንነት ስጋትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁጥር 7/2012 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤
2. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን የማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 42) ስለተፈጻሚነት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ዛሬ ......ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ**
ትግስት ሃሚድ
የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
ዋና ዳይሬክተር